

Ready for Pre-K!

# የቋንቋ እድገት ምንድን ነው?

- ፍላጎቶችን፣ የሚያስፈልጉትን፣ እና ሀሳቦችን መግለጽ
- የቃል እና የቃል-የሆነ ንግግርን መጠቀም
- የንግግር ቋንቋን መረዳት
- የእይታ መግባቢያን መረዳት
- ቀላል ትዕዛዞችን መከተል



## ለምን አስፈላጊ ሆነ?

በቋንቋ ጠንካራ መሰረት ያላቸው ልጆች ስሜታቸውን ማወቅ እና መግለጽ፣ ጓደኞች ማፍራት፣ የዕለት ተዕለት ተግባራትን እና ትዕዛዞችን መከተል፣ ታሪኮችን እና ትምህርቶችን መረዳት፣ ችግር መፍታት፣ እና የቅድመ ማንበብና መጻፍ ፅንሰ ሀሳቦችን የተሻለ መረዳት ይችላሉ።

## ለመርዳት ምን ማድረግ ይቻላል?

ለትንንሽ ልጆች የቋንቋ አጠቃቀምን እና ውጤታማ ግንኙነትን ሞዴል ማድረግ ኀይል አለው። ቀኑን ሙሉ ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ እና ወደ ኋላ እና ወደ ፊት (ማዳመጥ እና መናገር) ውይይት ላይ ይሳተፉ! በመጫወት፣ በመዘመር እና ታሪኮችን በማንበብ ለተለያዩ ቃላት ያጋልጧቸው! ልጆችዎ የሆነ ነገር ሲነግሩዎት ወይም የሚወዷቸውን ነገር ሲያሳዩዎት ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

ድህረገጻችን ይጎብኙ

# ቋንቋን ለመደገፍ የሚጠቀሙ ነገሮች



## የቃል–ያልሆኑ መልዕክቶች

- ከልጅዎ ጋር ሲነጋገሩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ወይም ምልክቶችን ይጠቀሙ።
- ትኩረትዎን ለመሳብ ልጅዎ ሲጠቁም ወይም እጅዎን ሲጎትት ምላሽ ይስጡ።
- እንደ የፊት ገጽታ ያሉ ስሜቶችን ለመለየት የቃል ያልሆነ መግባቢያ አስፈላጊነትን ልብ ይበሉ።



## ይድገሙ እና ያራዝሙ

- ልጆችዎ የሚሉትን (ወይም ለማለት የሚሞክሩትን ) ያዳምጡ።
- እነሱ የሚሉትን ይድገሙ፣ እና ሌላም ይጨምሩበት። የሚከተለውን ዓይነት…

  ልጅ፥ “ውሻ!”

  አዋቂ “አዎ፣ እርሱ ውሻ ነው ! ትልቅ ነጭ ውሻ!”



## የራስ ንግግር

ስለሚያደርጉት ነገር ይናገሩ እና ድርጊቶችዎን ይግለጹ። ይህ ከምግብ ማብሰያ ፕሮግራም አስተናጋጅ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል፣ ለምሳሌ፣ “አሁን ይህን ማንኪያ ሾርባውን ለማማሰል እየተጠቀምኩበት ነው!”



## የጎን ለጎን ንግግር

ተግባራቸውን በመተረክ ልጅዎ እያደረገ ስላለው ነገር ይናገሩ። ይህ ከስፖርት አዋቂ ጋር ተመሳሳይ ሊመስል ይችላል፣ ለምሳሌ፣ “ጣቶችዎን በመጫወቻው ላይ ቀዳዳዎችን ለመስራት እየተጠቀሙ ነው። አሁን በእጆችዎ መካከል እያንከባለሉት ነው።